# አስተዳደራዊ መግለጫ



ጃኑዋሪ 2014 ዓ.ም.

Seattle
Community
Police Commission

የኛ ከተማ። የኛ ደህንነት። የኛ ፖሊስ። አብሮ ይሻላል።

ለመገናኘት፡-

**Office of the Community Police Commission**
**PO Box 94765**
**Seattle, WA 98124-7065**
**206-233-2664**
**OCPC@seattle.gov**

**www.seattle.gov/policeCommission**
**አስተዳደራዊ መግለጫውና ሙሉው የ2014 ዓ.ም. ኮምዩኒቲ አሳታፊ ዘገባ ኢንተርኔት ላይ በሚከተለው አድራሻ ይገኛሉ፡-**
**www.seattle.gov/policeCommission/resources.htm/.**

# አስተዳደራዊ መግለጫ

## የሲያትል ማህበረሰብ ፖሊስ ኮሚሽንና ማህበረሰባዊ ተሳትፎ

የሲያትል ፖሊስ መምሪያ (SPD) በአሠራሩ ላይ ተከታታይ ሕገ መንግሥታዊ መተላለፎች እንደተገኙበት የዩኤስ ፍትሕ መምሪያ (DOJ) ከዘገበ በኋላ፣ በ2012 ዓ.ም. የሲያትል ከተማ አስተዳደር SPDን ለማሻሻል ከDOJ ጋር ስምምነት ውስጥ ገባ። ስምምነቱ የሲያትል ኮምዩኒቲ ፖሊስ ኮሚሽን (CPC) እንዲቋቋም ያዝ ነበር፣ ይህም የተለያየ አመለካከት ያላቸው የማህበረሰብ አባላትን ያዘለ ሲሆን ሚናቸውም የፖሊስ መምሪያ መሻሻል ሂደቱንና የማሻሻል ሐሳቦችን በተመለከተ ከማህበረሰቡ አስተያየት ያመጣሉ። CPC የሲያትልን ቅይጥ ማህበረሰቦች አሳትፎና አመለካከታቸውን ወክሎ፣ ድምጽ በመስጠት የፖሊስ አገልግሎቶችን የማሻሻል ዕድል ማካፈል ኃላፊነት አለበት።



Lisa Daugaard (ሊሳ ዶጋርድ)፣ ረዳት ሊቀመንበር፣ Diane Narasaki (ዳያን ናራሳኪ)፣ ረዳት ሊቀመንበር፣ Claudia D'Allegri (ክሎዲያ ዳለርጂ)፣
Bill Hobson (ቢል ሆብሰን)፣ Jay Hollingsworth (ጄይ ሆሊንግስወርዝ)፣ Kate Joncas (ኬት ጆንካስ)፣ Joseph Kessler(ጆሴፍ ኬስለር)፣
Tina Podlodowski (ቲና ፖድሎዶስኪ)፣ Marcel Purnell (ማርሴል ፐርኔል)፣ Jennifer Shaw (ጄኒፈር ሾ)፣ Kevin Stuckey (ኬቨን ስተኪ)፣
Rev. Harriett Walden (ሬቨረንድ ሃሪዬት ዎልደን)፣ Rev. Aaron Williams (ሬቨረንድ አረን ዊሊያምስ)

ኃይልን መጠቀም እንዲሁም በመኪና ውስጥ ቪዲዮ ከመቅዳት ጋር በተያያዘ ረቂቅ ፖሊሲ ሐሳቦችን አስተያየት ለመቀበል ነበር። የተገኘው አስተያየት CPC በኖቬምበር 15፣ 2013 ዓ.ም. ያደረገው የፖሊሲ ሐሳብ ዘገባ ውስጥ ተካትቶ ነበር። በዚሁ በ2013 ዓ.ም. በተደረገው የማሳተፍ ጥረት ላይ CPC ስለማሻሻል ሂደቱ ባጠቃላይ፣ ስለ CPC ሚና፣ ከፖሊስ ጋር ስላለው ገጠመኝና ለወደፊት የማህበረሰብ ተሳትፎ እንቅስቃሴዎችን በተመለከተ የማህበረሰቡን አመለካከት ለመሰብሰብ ሞክሯል።

የማህበረሰቡ ተሳትፎ ደረጃ አስደናቂ ነበር። የተሳተፉት ግለሰቦች እንዲሳተፉ ጥያቄ ስለቀረበላቸው ደስታቸውን ገልጸው ወደፊትም ውይይቱን ለመቀጠል ከፍተኛ ፍላጎት እንዳላቸው ተናግረዋል። ሆኖም የሂደቱ የጊዜ ጥበቶች ብዙ እንቅፋት ያስከተሉ ሲሆን አንዳንድ አስፈላጊ አጋር ድርጅቶችና አካላት ሙሉ በሙሉ ከመሳተፍም አግዷቸዋል። የጊዜ ገደቡም SPD የሚከተላቸውን የመጨረሻ ፖሊሲዎችና መሻሻሎች ላይ እውነት የማህበረሰቡ አስተያየት ተጽእኖ ለማምጣቱ ጥርጣሬ አሳድሯል።

የማሻሻሉ ሂደት ላይ መተማመን የሚመጣው በተጨባጭ ለውጥ ሲታይ እንደሆነ ተሳታፊዎች በግልጽ አሳውቀዋል። የሂደት ዘገባን እንዲሁም CPC የሚያቀርባቸው ሐሳቦች አዳዲስ ፖሊሲዎች ውስጥ መካተታቸውን የሚያሳይ ዘገባን፤ የማህበረሰቡ አስተያየት የመጨረሻ ፖሊሲዎች ላይና ባጠቃላይ የማሻሻል ጥረቶች ላይ ምን ያክል ተጽዕኖ እንዳስከተለ የሚገልጽ መረጃ፣ እና ዓመታዊ የማህበረሰብ መጠይቅ ውጤቶችን የሚያካትት ውይይት ከማህበረሰቡ ጋር በቀጣይነት ማድረግ ያስፈላጋል።

Office of Professional Accountability Auditorን (የሙያ ተጠያቂነት ኦዲተር ቢሮ) እና Seattle Human Rights Commissionን (ሲያትል ሰብዓዊ መብት ኮሚሽን) ጨምሮ። ሥራችንን በምንቀጥልበት ወቅት ወደፊት ሌሎች ትብብሮችንንም በጉጉት እንጠብቃለን።

## በኦክቶበር 2013 ዓ.ም. CPC፣ አጋሮቹና ደጋፊዎቹ ከ150 በላይ በሚሆኑ ስብሰባዎች ላይ ከ3400 በላይ የማህበረሰብ አባላት አሰባስበው ነበር።


ተሳታፊዎች ሕዝቡ መብቱን በተመለከተ፣ ቅሬታዎችን ማስገባት በተመለከተ፣ የፖሊስ ተጠያቂነት ሥርዓት አሠራርንና የመሻሻል ሂደቱን በተመለከተ መረጃ የማግኘት ጉጉት እንዳለውም ያምናሉ።

CPC የማህበረሰቡንና የፖሊስ ግንኙነትን ማሻሻያ መንገዶችን ለመፈለግ ውይይቶችን በማካሄድ የማህበረሰቡን አስተያየት መጠየቁን ይቀጥላል፣ በተለያዩ የፖሊሲ ጉዳዮች ላይ የማህበረሰቡን አመለካከትም ያቀርባል።




በ2013 ዓ.ም. የ CPC ፖሊሲ ሥራ ቡድኖች የብዙ ግለሰቦች ትብብርና ቴክኒካዊ እርዳታ አግኝተዋል፣ የ DOJ እና U.S. Attorney's Office (ዩ ኤስ አቃቤ ሕግ ቢሮ)ን፣ SPD ን (በተለይ ከደንብ አስከባሪ ቡድንና ከኦዲተ፣ ፖሊስና ከለሳ ሠራተኞች)፣ Washington State Criminal Justice Training Commissionን (የዋሽንግተን ስቴት ፍትሕ ሥልጠና ኮሚሽን)፣






# በ2013 ዓ.ም. ማህበረሰብ የማሳተፍ ሂደት

CPC የጠቅላላ ሕዝቡን፣ የፖሊሶችንና የሠራተኛ ማህበራቸውን ተወካዮች እንዲሁም ሌሎች ቁልፍ መንግሥታዊ የግለሰብ አባላት በማሻሻል ሂደቱ ላይ ያላቸውን አመለካከት ለማግኘት ቢሞክርም ኮሚሽነሮቹ ግን የፈለጉት በተለይ በሲያትል ውስጥ ከ SPD ጋር ግጭት የነበራቸውን ወይም በፖሊሲ መቅረጽ ሂደቱ ላይ በታሪክ አነስተኛ ተወካይነት የነበራቸውን አመለካከት ነው።

CPC እነዚህን አነስተኛ ተወካይነት የነበራቸውን የኮምዩኒቲ አባላት ደህንነቱ በተጠበቀ መድረክ ላይ ጠርቶ በፖሊስ ማሻሻያው ላይ አስተያየት እንዲያቀርቡ ልዩ ጥረት አድርጎ ነበር፣ ይህንንም ያደረገው በቀላሉ የማይገኙ ሕዝቦችን በቀጥታ የሚያገለግሉ 13 በኮምዩኒቲ ላይ የተመሠረቱ ድርጅቶችን በመገናኘትና ሌሎችንም በማነጋገር ነበር። በዚህ ጥረት ላይ ባጠቃላይ ከ100 ድርጅቶች በላይ ተሳትፈው ነበር።

CPC፣ አጋሮቹና ደጋፊዎቹ ከ150 በላይ በሚሆኑ ስብሰባዎች ላይ ከ3400 በላይ የማህበረሰብ አባላት አሰባስበው ነበር። ጥራቱንም ብዛቱንም በተመለከተ አስተያየት ደርሶት ነበር - ተሳታፊዎች ከ3000 በላይ መጠይቆች ሞልተው፣ የስብሰባ አዘጋጆችም በውይይቶች ላይ የተነሱትን ቁልፍ ነጥቦች በሰፊው መዝግበው ነበር። አብዛኛው መጠይቆች በእንግሊዝኛ ሲሆን የተሞሉት፣ ሌሎች 464 ከእንግሊዝኛ ቋንቋ ውጪ የተሞሉ መጠይቆች ተተርጉመው ነበር።

## የመጠይቅ ውጤቶች

የ CPC መጠይቅ የተዘጋጀው ሰፋ ያለ ተሳትፎ ለማስተናገድ ነበር፣ ሲያትል ውስጥ የሚኖሩትንና የሚሠሩትን ሁሉ አስተያየት በቁጥር ወከሎ ለማስቀመጥ የተዘጋጀ አልነበረም። ለማወዳደር እንዲያመች፣ ብዙዎቹ የCPC ጥያቄዎች ባለፈው ዓመት በሲያትል ውስጥ የፖሊስ መሻሻል ስምምነትን ሲቆጣጠር በነበረው በፌዴራል ሞኒተር ትእዛዝ መሠረት ከቀረቡት ጥያቄዎች ጋር ተመሳሳይ ናቸው። የ CPC መጠይቅ ተጨማሪ ጥያቄዎች ያቀረበ ሲሆን ስለ መልስ ሰጪዎች በይበልጥ ሥነ-ሕዝባዊ መረጃ ይጠይቅ ነበር። በእንግሊዝኛና በስልክ የተካሄደው የሞኒተር መጠይቅ ጠቃሚ መረጃ እና የሲያትል ሕዝብን አጠቃላይ አስተያየት ያቀርባል። ሆኖም በይበልጥ የተሟላ የማህበረሰብ አስተሳሰብን የሚያንጸባርቅ እይታ ለመስጠት ከዚህ ቀደም ሐሳባቸው ያልተሰማ፣ ከፖሊስ አሠራር ጋር አለመስማማት ሊኖራቸው የሚችሉ ሰዎች በእኩልነት መሳተፋቸውን ለማረጋገጥ ሌሎች መድረኮች ማዘጋጀቱ አስፈላጊ ነው ብሎ CPC አመነ።

በዚህም ምክንያት የ CPC መጠይቆች የተዘጋጁት በተለያዩ ቋንቋዎች ሆኖ ስብሰባዎቹ የተካሄዱት የተገፋው ማህበረሰብ መካከል ሲሆን አቅራቢዎቹም የሚታመኑ የማህበረሰርቡ መሪዎች ነበሩ። የአእምሮ ሕመምተኞችና ሌሎች የአካል ጉዳት ያለባቸውም ሰዎች ሐሳባቸውን ማካፈል እንዲችሉ ልዩ ጥንቃቄ ተደርጎ ነበር። ማህበረሰቡ ስለ SPD ያለውን አመለካከት ሙሉ በሙሉ ለማንጸባረቅ የ CPC መጠይቅ ውጤቶች ጠቀሜታ እንደሚሰጡ ሞኒተር ተስማምቷል።

## ሥነ-ሕዝብ

CPC አነስተኛ ተወካይነት ያላቸውን ብዙ ሰዎች የማግኘቱን ግቡን በስኬታማ መንገድ አሟልቷል። ከመጠይቆቹ ሰባ ሁለት በመቶው (72%) የተሞሉት የተለያየ ጎሳ ባላቸው ሰዎች ነው። (ኮሚሽኑ “የተለያየ ጎሳ” የሚለው የተለያየ ፍቺ ሊሰጠው የሚችል እንደሆነ ቢያውቅም፣ በዚህ ጉዳይ ላይ ነጭ ያልሆኑ ሰዎችን ለመግለጽ ነው።) ከ24% በላይ ስደተኛ ወይም ጥገኛ ናቸው። አሥራ ሁለት በመቶው (12%) ዕድሜያቸው ከ18 በታች ሲሆን፣ 18% ዕድሜያቸው በ18 እና 25 መካከል ነው፣ 23% ደግሞ ዕድሜያቸው 56 ዓመት ወይም ከዛ በላይ የሆኑ ናቸው። በወንዶች እና በሴቶች መካከል የነበረው ልዩነት ተቀራራቢ ሲሆን (49% እና 48%)፣ 1% በጾታ መካከል የሆኑ ናቸው። 16% የሚሆኑት ግብረ ሶዶም፣ ዘማ እና ከሴትም ከወንድም የሚሆኑ ናቸው።

## የመስተንግዶ እኩልነት

አብዛኞቹ (68%) የተለየ ዘርና ጎሳ ያላቸውን ሰዎች SPD በእኩልነት አያስተናግድም ብለው ሲያምኑ 65% ደግሞ SPD የሲያትል አካባቢዎችን በሙሉ በእኩልነት ያስተናግዳል ብለው አያምኑም። ሁለት ሶስተኛዎቹ ወይም ከዛ በላይ የሚሆኑት የሲያትል ፖሊሶች ቤት አልባዎችን ወይም ከዚህ በፊት ወንጀል የሠሩ ሰዎችን ከሌሎች እኩል አያስተናግዱም ብለው ያምናሉ። ከ50% በላይ የሚሆኑት የአእምሮ ሕመም ወይም የአልኮልና የእጽ ሱስ ያለባቸው ሰዎች፣ ወጣቶች፣ የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች ወይም የቅርብ ምሥራቅ ዝርያ ያለባቸው ሰዎች በእኩልነት መስተንግዶ አያገኙም ብለው ያስባሉ፣ ከ40% በላይ የሚሆኑት ደግሞ LGBTዎች እንደ ሌሎች ጥሩ መስተንግዶ አያገኙም ብለው ያምናሉ።

መላሾች ባጠቃላይ ፖሊሶች ባብዛኛው አሉታዊ ተግባሮች ላይ ሲሰማሩ ይታያሉ ብለው ያምናሉ። ከፍተኛዎቹ ውጤቶች ያተኮሩት ሰዎችን በዘራቸው ልዩነት ምክንያት የተለየ መስተንግዶ መስጠት - 73%፣ በዘር አድሎ የተመሠረተ እርምጃ መውሰድ - 69% እና ከመጠን በላይ አካላዊ ኃይል መጠቀም - 60% ናቸው። የቀሩት አሉታዊ አኳኋኖች በሙሉ ከሁለት በስተቀር ከ50% በላይ ውጤት አምጥተዋል።

## ከ SPD ጋር ግንኙትና የተጠያቂነት ሂደት

ወደ አንድ ሶስተኛየሚሆኑት መላሾች ለ SPD አቤቱታ አቅርበው ከእነርሱ ውስጥ 57%ው በ SPD መስተንግዶ አልተደሰቱም። ወደ ሁለት ሶስተኛ (64%) የሚሆኑት እራሳቸው ወይም ቤተሰባቸው ከ SPD ጋር በግል ገጠመኝ ኖሯቸው፣ 60%ው አሉታዊ እንደነበር ገልጸዋል። ከ SPD ጋር ገጠመኝ የነበራቸው ሰዎች አስተያየት እንዲጽፉ ክፍት ጥያቄ ተጠይቀው 71%ው ሙሉ በሙሉ መልሰዋል። ወደ ግማሽ የሚሆኑት (48%) አስተያየቶች አሉታዊ ስሜት እንዳላቸው ያሳያሉ። አብዛኞቹ አስተያየቶች ፖሊሶች በአካልም በቃልም ኃይለኛ እንደሆኑ (14%)፣ ክብር የጎደላቸው እንደሆኑ (13%) እና የፖሊስ አድሎ እንዳለ (12%) ገልጸዋል።



የማህበረሰብ ስብሰባዎች ላይ የተሳተፉ ሰዎች SPD ውስጥ ምን ምን መቀየር እንዳለበት ለይተው ሐሳብና መፍትሔዎች አቅርበዋል፣ የ CPC ረቂቅ ፖሊሲ ላይም አስተያየት ሰጥተዋል።

## የ SPDን ክንውን ማሻሻያ ፖሊሲዎች

መጠይቁ የ SPD ክንውንን ማሻሻል በተመለከተም አንድ ጥያቄ ይዞ ነበር። ብዙዎቹ የ CPC ረቂቅ ፖሊሲ ሐሳቦች ውስጥ የተካተቱት ጉዳዮችን በተመለከተ አስተያየት ሰጥተዋል። ብዙዎቹ (ከ75% እስከ 88%) እነዚህ እርምጃዎች ለውጥ ያመጣሉ ብለው ያስባሉ።

## አጠቃላይ ግኝቶች

መላሾች ስለፖሊስ በርካታ አሉታዊ አመለካከቶች ቢኖራቸውም የሰዎችን ደህንነት በመጠበቅ፣ ሰፈራቸውን በማገልገልና ሰዎችን በአክብሮት በማስተናገድ ባጠቃላይ ከፍተኛ ውጤት ሰጥተዋቸዋል። ባጭሩ ፖሊሶች በማህበረሰቡ ውስጥ ሥራቸውን በመሥራት በደፈናው ስኬታማ ናቸው ብለው መላሾች ቢያምኑም፣ ብዙ መጠይቁን የሞሉ መላሾች ግን SPD አንዳንድ ሰዎችን በእኩልነት እንደማያስተናግድና የ SPD ፖሊሶችም ብዙ አሉታዊ ተግባሮች ሲያከናውኑ እንደሚታዩ ያምናሉ።

## በማህበረሰርብ ስብሰባዎች ላይ ቁልፍ ርእሶች

የማህበረሰብ ስብሰባዎች ላይ የተሳተፉ ሰዎች SPD ውስጥ ምን ምን መቀየር እንዳለበት ለይተው ሐሳብና መፍትሔዎች አቅርበዋል፣ የ CPC ረቂቅ ፖሊሲ ላይም አስተያየት ሰጥተዋል። በስብሰባዎች ላይ የተነሱ ዋና ርእሶች ከመጠይቁ ግኝቶች ጋር ወጥ ነበሩ። ሰዎች በነበራቸው ገጠመኞች ላይ ተመሥርተው SPD ላይ ጥልቅ የሆነ ጥርጣሬ እንዳላቸው ይታያል፣ ይህም አንዳንድ ፖሊሶች አድሎ ስለሚያሳዩ፣ ሰዎችን ያለአግባብ ስለሚያስቆሙ፣ አላስፈላጊ ኃይል ስለሚጠቀሙና አንዳይከሰሱ መኪና ውስጥ ባለ መቅጃ ቪዲዮ በትክክል ስለማይጠቀሙ ነው።

## አድሎ

ስብሰባዎቹ ላይ የተሳተፉ ሰዎች ፖሊስ አድሎ የሚያሳየው በዘር ተመሥርቶ እርምጃ በመውሰድ፣ ለሌሎች ባሕሎችን ባለመረዳትና ባለመቀበል፣ አክብሮት በማጣት፣ በማስፈራራትና በማሸማቀቅ ነው ብለው ያምናሉ። ፖሊሶች ለአንዳንድ የወንጀል ተጠቂዎች አይደርሱም፣ አንዳንድ ሰፈሮችም ዝቅተኛ አገልግሎት ያገኛሉ ብለው ያምናሉ - ይህም የሚሆነው በግል አድሎ ምክንያት ወይም አድሎ የተመላበት ውጤት በሚያስከትል አሠራር ምክንያት ነው። ሁለገብ መሠረት ያላቸው ፖሊሶችን ለመቅጠርና ፖሊሶች የተለያዩ ሰዎችን በደንብ ማስተናገድ የሚያስችሏቸው ውጤታማ ባሕላዊ ግንዛቤና ሌሎች ሥልጠናዎችን (ማለትም የቀውስ ማስወገድ) ለማካሄድ ከፍተኛ ድጋፍ ነበር። በተጨማሪም SPD ውስጥ አድሎን መቀነስ እንዲቻል አቤቱታዎችን ለመከታተል ጠንካራ የተጠያቂነት ሥርዓት ለመዘርጋትና መረጃ ሰብስቦ ስኬታማነትን ለመለካት ጠንካራ ድጋፍ ነበር። የ CPC ፖሊሲ ላይ ከቀረቡት ሐሳቦች ውስጥ ከአድሎ ነጻ የሆነ የፖሊስ ሥራ ትግባር ላይ ማዋል ከፍተኛ ድጋፍ አለ፣ አንዳንዶችም የማህበረሰብ አባሎች መብታቸውን እንዲያውቁና የአድሎ አቤቱታ ሲኖራቸው እንዴት ይግባኝ እንዲሚሉ እንዲሁም አብሮ የሚሄደውን የምርመራ ሂደት እንዲያውቁ ትምህርት መስጠት ያስፈልጋል ብለዋል።



## ማስቆምና ማሠር

ብዙ ሰዎች አንዳንዶች በዘር ላይ በተመሠረተ አድሎ ምክንያት፣ ግብታዊ አቋም፣ ባሕል ባለማወቅ፣ የወንጀለኝነት ታሪክ ወይም ሌሎች አግባብ በሌላቸው ምክንያቶች ያለአግባብ እንደሚያስቆሙ ያምናሉ። ፖሊሶች ለማስቆምና ለማሠር የተሰጣቸውን ሥልጣን ገደብ አይረዱም፣ እንዲሁም ብዙ የማህበረሰቡ አባላት በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታዎች ላይ ያሏቸውን መብቶች አያውቁም ብለው ያምናሉ። በዚህ ጉዳይ ላይ ሕዝቡን የማስተማርና ለፖሊሶች መብታቸውንና ግዴታቸውን በተመለከተ ሥልጠና መስጠት፣ እንዲሁም ሰውን በሚያስቆሙበት ሰዓት ምን ማድረግ እንዳለባቸው ማሳወቅ በጣም አስፈላጊ ነው ብለው ያምናሉ። ብዙ ተሳታፊዎች ስለ CPC ፖሊሲ ሐሳብ አቅርቦት (ለማስቆም ያለውን ሕግ ግልጽ ማድረግ) አዎንታዊ አመለካከት ቢኖራቸውም አንዳንዶቹ ችግሩን በትክክል አይፈታም ብለው ሰግተዋል። CPC ባቀረበው ጸረ-አድሎ የፖሊስ ሥራ ፖሊሲ ውስጥ በቀረበው መሠረት፣ ፖሊስ ባስቆመ ቁጥር መመዝገብ ትክክል ያልሆነ መስተንግዶን ለመለየት ያስችላል ለሚለው ድጋፍ አለ።

## ከፍተኛ ኃይልን መጠቀም

ብዙ ጊዜ ፖሊሶች ሳያስፈልግ ከፍተኛ ኃይልን ይጠቀማሉ የሚል ሐሳብ አለ፣ አንዳንድ ጊዜ በማስጨነቅ ወይም በማጥቃት ሁኔታዎችንም ያባብሳሉ። ብዙዎቹ በግል ይህ እንዳጋጠማቸው ወይም በራሳቸው ማህበረሰብ ውስጥ የተከሰተ ሁኔታ እንደሚያውቁ ገልጸዋል። የተሰነዘሩት መፍትሔዎች የሚያተኩሩት ፖሊሶች አስቸጋሪ ግለሰቦችን እንዴት እንደሚያስተናግዱ ሥልጠና መስጠት ላይ፣ ሁኔታዎችን ማርገብ ላይ እና ኃይል አጠቃቀምንና ይግባኝ ማለትን በተመለከተ ለሕዝቡ ትምህርት መስጠት ላይ ነው። ፖሊሶችን ለመቅጠርና ቀጣይ ድጋፍ ለመስጠትም የተወሰኑ ስልቶች በሐሳብ ደረጃ ቀርበው ነበር። SPD ያቀረበው ፖሊሲ የተወሳሰበ ስለሆነ በይበልጥ ግልጽ በሆነ መንገድ ተሻሽሎ ቢቀርብ ለፖሊሶችም ሆነ ለሕዝቡ በይበልጥ ጠቃሚ እንደሚሆን ብዙዎቹ ገልጸዋል። SPD ፖሊሲው ላይ ያቀረበውን ኃይል የተጠቀሙባቸውን አብዛኞዎቹን ሁኔታዎች ከመዘገብና ምርመራ ከማካሄድ ጋር በተያያዘ ተሳታፊዎች ድጋፋቸውን የገለጹ ቢሆንም አንዳንዶች አነስተኛ ኃይል የተጠቀሙባቸው ሁኔታዎችም መመዝገብና መመርመር አለባቸው ብለው ያምናሉ። ተሳታፊዎች ሌሎች ተጨማሪ የፖሊሲ ሐሳቦች አቅርበው ነበር፣ ማህበራዊ ጸጥታን ማናጋት ላይም ኃይል የመጠቀምና የማርገብ መስፈርቶች ፖሊሲው እንዲያቋቁምም ጨምረው ተናግረዋል።

### መኪና ውስጥ ቪዲዮ መቅዳት

መኪና ውስጥ የተቀዱ ቪዲዮዎችን ፖሊሶች መጠቀማቸውን በተመለከተ የማህበረሰቡ አባላት ከፍተኛ ጥርጣሬ ገልጸዋል። ብዙዎቹ በፖሊሶች ውሳኔ መቀዳቱ በጣም ውስን እንዲሆን ይፈልጋሉ (ካሜራዎች አውቶማቲክ ሆነው በራሳቸው እንዲቀዱ በይበልጥ የሚፈለግ ሲሆን አንዳንዶች ደግሞ ካሜራው ሁልጊዜ እንዲበራ ይፈልጋሉ)። ካሜራው ሰው አብርቶትም ሆነ በራሱ በርቶ እንዴት እንደሚቀዳና እንዲሁም ፖሊሶች የሚወስዷቸውን እርምጃዎች የመመዝገብ መብት እንዳለው ሕዝቡ እንዲረዳ በማህበረሰብ ደረጃ ትምህርት ማስፈለጉ ትኩረት ተሰጥቶታል። ደንብ የማክበርና የቅጂ ፖሊሲዎች መከበራቸውን ለማረጋገጥ ውጤታማ የሆነ የተጠያቂነት ሥርዓት እንደሚያስፈልግ ብዙዎቹ ድጋፋቸውን ገልጸዋል። አብዛኞቹ CPC ያቀረባቸውን ሐሳቦች የደገፉ ሲሆን ወጥና ታማኝ ቅጂዎች ለፖሊሶችም ሆነ ለሕዝቡ ጠቃሚ እንደሆኑ ያምናሉ። በተለይ የፖሊስ መኪና ለማይዙ ፖሊሶች አካል ላይ የሚጠመዱ ካሜራዎች ጥቅም ይኖራቸው እንደሆነ በ SPD እንዲታይ አንዳንዶች ሐሳብ ያቀረቡ ሲሆን፣ ቅጂዎቹ በቀላሉ መገኘታቸው አስፈላጊ ቢሆንም ብዙዎች በምስጢር የመያዛቸውን መብት በተመለከተ ስጋታቸውን ገልጸው ይህንን ከባድ ርእስ ፖሊሲው እንዲፈታው ሐሳብ አቅርበዋል።

### ለወደፊት ለውጦች የቀረቡ ሐሳቦች

ሒስ ቢኖርም ተሳታፊዎች ስለ SPD ፖሊሶች ብዙ አዎንታዊ አስተያየቶች አካፍለው በርካታ መሻሻል ስለሚገባቸውም ነገሮች ሐሳብ አካፍለዋል። አንዳንድ ተሳታፊዎች ከ SPD ፖሊስ ጋር የነበሯቸውን አክብሮት የተመላባቸው ገጠመኞችም ተናግረዋል። አንዳንዶችም እንዳሳሰቡት አንድ “መጥፎ” ፖሊስ የመላ መምሪያውን ስም ሊያበላሽ ይችላል፤ ሌሎች እንዳሳሰቡት ደግሞ ሌሎች ግዛቶች ውስጥ ደካማ ባህርይ ያላቸው ፖሊሶች መኖር የ SPD ፖሊሶችን ስም ሊያጠፉ ይችላል። የተወሰኑ ወጣቶች ስለሚያምኗቸውና ጥሩ መስተናግዶ ስላደረጉላቸው ፖሊሶች ተናገሩ - እነዚህ ፖሊሶች በአኳኋናቸው አክብሮት አሳይተው እንደሚቀርቁሩ ገልጸዋል፣ በተጨማሪም ለመርዳት ዝግጁ እንደሆኑና እነዚህ ወጣቶች ያሏቸውን ችግሮች እንደሚረዱ አሳውቀዋል። ደግሞ ደጋግሞ የተነሳ ርእስ ቢኖር ፖሊሶች በሲያትል ውስጥ ካሉት የተለያዩ ማህበረሰርቦች ጋር ግንኙነት መፍጠር እንዳለባቸው ነው። ከሚያገለግሏቸው ማህበረሰቦች ጋር የተሻለ መቀራረብ ለመጀመር ምን ማድረግ እንደሚችሉ የተለያዩ ሐሳቦች ቀርበው ነበር። ዛሬ የተዘረጉ መደበኛ ጣቢያዎች እነዚህን መቀራረቦች ሙሉ በሙሉ ስለማያገለግሉ ግንኙነቶቹ ማጠናከሪያ ይሆናሉ።

## ወቅታዊ ሁኔታና ለ2014 ዓ.ም. ቀጣይ እርምጃዎች

### ማህበረሰርብ ማሳተፍ ዘገባ

በ2013 ዓ.ም. ማህበረሰብን ማሳተፍ በተመለከተ CPC የነበሩትን እንቅስቃሴዎችና ውጤቶቻቸው ለስምምነቱ አካላትና ለሌሎች በሲያትል ለሕዝብ ደህንነትና ለፖሊስ ተጠያቂነት ከፍተኛ ፍላጎትና ኃላፊነት ለነበራቸው ይሰጣል፣ ይህንን አሳታፊ እንቅስቃሴ ለማድረግ ከ CPC ጋር አብረው ለሠሩ ድርጅቶችና ግለሰቦች ጨምሮ።

### የጸደቁ ፖሊሲዎች ክለሳ

ፍርድ ቤቱ ለ SPD አዲስ የኃይል አጠቃቀም ፖሊሲና ከአድሎ ነጻ የሆነ አሠራርን፣ ማስቆምና ማሠርን እንዲሁም በመኪና ውስጥ ቪዲዮ መቅዳትን በተመለከተ የመጨረሻ ፖሊሲዎች ከአሁኑ ያጸደቀ ሲሆን በ2014 ዓ.ም. መጀመሪያ ላይ በሥራ ላይ ይውላሉ። CPC የጸደቁትን ፖሊሲዎች ይከልስና CPC ካቀረባቸው ቁልፍ አቅራቦቶች ምን ያክሉ እንደተካተቱ፣ ሁለቱ እንዴት እንደሚነጻጸሩና ስለ አዲሱ የፖሊሲ ማውጫ ሂደት ግምገማ አድርጎ ለማህበረሰቡ ዘገባ ያቀርባል።

**CPC የጸደቁትን ፖሊሲዎች ይከልስና CPC ካቀረባቸው ቁልፍ አቅራቦቶች ምን ያክሉ እንደተካተቱ፣ ሁለቱ እንዴት እንደሚነጻጸሩና ስለ አዲሱ የፖሊሲ ማውጫ ሂደት ግምገማ አድርጎ ለማህበረሰቡ ዘገባ ያቀርባል።**

## ቁልፍ ፖሊሲዎችን በተመለከተ ስለ SPD ሥልጠና ክለሳና የቀረቡ ሐሳቦች

በ2014 ዓ.ም. ካድሎ ነጻ የሆነ የፖሊስ አሠራር፣ ማስቆምና ማሠር፣ ኃይል መጠቀምና ችግር መወጣትን በተመለከተ CPC ማሠልጠኛ የትምህርት ሥርዓትና ተያያዥ ርእሶች ሐሳቦች ያቀርባል። CPC ሐሳቦቹን ማቅረብ ያለበት የቀን ገደቦች ይለያያሉ፣ አንዳንዶቹ በዓመቱ መጀመሪያ ሩብ ዓመት ውስጥ ሲሆን ሌሎቹ ደግሞ በሁለተኛው ሩብ ዓመት ውስጥ ይሆናል።

## ደንብ የማስከበር ሂደቶችን በተመለከተ የመረጃ ትንተናና የሐሳብ አቅርቦቶች

አዲሱን ከአድሎ ነጻ የፖሊስ ሥራ ፖሊሲን በማስከተል SPD ከ SPD ጋር በመተባበር የትኛው ዘርና ብሔር ላይ አላግባብ ከፍተኛ ሕግ ማስከበር እንደሚከሰት ይለያል፣ አድሎ የሌለው ውጤት የሚያስገኙ ሌሎች ውጤታማ አሠራሮች ምን እንደሆኑም ያጠናል። ከ CPC ጋር አብረው የሚሠሩ ተመራማሪዎች የ SPDን የእሥራት፣ ማስቆም፣ ማቆየት፣ ቲኬት መስጠትና ኃይል መጠቀም መረጃን በዛ ዕቅድ ውስጥ ይተነትናሉ።

## ስለ SPD ተጠያቂነት ክለሳና የቀረቡ ሐሳቦች

CPC የ SPDን ተጠያቂነት ሥርዓትም ይከልሳል፣ የ Office of Professional Accountability (OPA) (የሙያ ተጠያቂነት ቢሮ) ፖሊሲዎች፣ መዋቅርና ሂደቶችንም ጨምሮ። እስከ ኤፕሪል 30 ቀን ድረስ ሐሳቦችን ያቀርባል። CPC የጸደቁትን ፖሊሲዎች ይከልስና CPC ካቀረባቸው ቁልፍ አቅራቦቶች ምን ያክሉ እንደተካተቱ፣ ሁለቱ እንዴት እንደሚነጻጸሩና ስለ አዲሱ የፖሊሲ ማውጫ ሂደት ግምገማ አድርጎ ለማህበረሰቡ ዘገባ ያቀርባል።

## የSPD አሳታፊ እንቅስቃሴዎች ክለሳና የቀረቡ ሐሳቦች

CPC ስለ SPD የማህበረሰብ አሳታፊ እንቅስቃሴዎች ዘገባ የማቅረብ ኃላፊነትም ያለበት ሲሆን የሕዝቡን መተማመን ከፍ ለማድረግ መምሪያው ሊጠቀማቸው ስለሚችለው ስልቶች አንዳንድ ሐሳብ ሊያቀርብም ይችላል። ይህ ሥራ በ2014 ዓ.ም. ውስጥ መቼ ማለቅ እንዳለበት አልተወሰነም።

### የሥራ ቡድን አባሎች

**ማህበረሰርብ አሳታፊ የሥራ ቡድን**

Claudia D’Allegri (ክሎዲያ ዳሌግሪ) እና
Kate Joncas (ኬት ጆንካስ)፣ ረዳት ሊቀመንበሮች
Jay Hollingsworth (ጄይ ሆሊንግስወርዝ)
Diane Narasaki (ዳያን ናራሳኪ)
Rev. Harriett Walden (ሬቨረንድ ሃሪዬት ዎልደን)

**ከአድሎ ነጻ የሆነ የፖሊስ አሠራር የሥራ ቡድን**

Jay Hollingsworth (ጄይ ሆሊንግስወርዝ) እና
Rev. Harriett Walden (ሬቨረንድ ሃሪዬት ዎልደን)፣ ረዳት ሊቀመንበሮች
Claudia D’Allegri (ክሎዲያ ዳሌግሪ)
Lisa Daugaard (ሊሳ ዶጋርድ)
Marcel Purnell (ማርሴል ፐርኔል)

**የማስቆምና ማሠር የሥራ ቡድን**

Bill Hobson (ቢል ሆብሰን) እና
Jennifer Shaw (ጄኒፈር ሾ)፣ ረዳት ሊቀመንበሮች
Lisa Daugaard (ሊሳ ዶጋርድ)
Kate Joncas (ኬት ጆንካስ)
Joseph Kessler (ጆሴፍ ኬስለር)
Kevin Stuckey (ኬቨን ስተኪ)
Rev. Aaron Williams (ሬቨረንድ አረን ዊሊያምስ)

**የኃይል መጠቀም ሥራ ቡድን**

Joseph Kessler (ጆሴፍ ኬስለር) እና
Rev. Aaron Williams (ሬቨረንድ አረን ዊሊያምስ)፣ ረዳት ሊቀመንበሮች
Jay Hollingsworth (ጄይ ሆሊንግስወርዝ)
Kate Joncas (ኬት ጆንካስ)
Jennifer Shaw (ጄኒፈር ሾ)
Kevin Stuckey (ኬቨን ስተኪ)
Rev. Harriett Walden (ሬቨረንድ ሃሪዬት ዎልደን)